


# *ክህደት በደም መሬት*

*በዳዊት ወ/ጊዮርጊስ*

***ሁሉም ኢትዮጵያዊ/ት ሊኖረው/ራት የሚገባ አንድ መፅሐፍ***

*መጽሐፉ ልዩ ልዩ የውስጥና የውጭ ኃይሎች በኢትዮጵያና ኢትዮጵያ ኃይሎች ጋራ በየምዕራፉ ትንቅንቅ ገጥመው የነበሩ ኢትዮጵያውያን ለአንድነታቸውና ለነፃነታቸው ያካሄዱት ታጋድሎ ይዘክራል፡፡ ከውጭ ኃይሎችና ወራሪዎች እንዲሁም ከቅጥረኞቻቸውና ከሀገር በቀል ከሃዲዎች ጋር ያተደረጉት ፍልሚያዎችና ትግሎች፥ ኢትዮጵያውያን የከፈሉትን ከባድ መስዋዕትነት፥ በየምዕራፉ የታየው ጀግንነት ፥ የድልና የሽንፈቶች ፍርርቆሽ፥ የመሪዎችን ከባድ ከባድ ስህተቶችን፥ በዚህም ሳቢያ የደረሱ ፓለቲካዊና ወታደራዊ ሽንፈቶችና ውድቀቶች አመጣጥ ያሳያል፡፡ የሀገር ህልውናና ደህንነት ቁልፍ ችግሮች --አባይ ፥ ቀይ ባህርና ኦጋዴን-- ሆነው የቆዩትን በሰፊው ይዳስሳል ፡፡ በየምዕራፉ ከገጠሙ ሽንፈቶችና ውድቀቶች ጋር የተያያዙ ክህደቶችን ያነሳል ፡፡ ለመሆኑ እነ ኢሳያስ አፈወርቂ ማንናቸው? መለስ ዜናዊስ? ፥ ሀይሎም አርአያ ፥ ሳሞራ የኑስ ቱባ ቱባ የወያኔ መሪዎች ባለፉት 35 ዓመታት የት ቦታ መቼና ምን አደረጉ? መፅሐፉ ስለነዚህ ግለሰቦች አነሳስና ማንነት የሚለው አለው፡፡ በአንፃሩ ኤርትራዊ ኢትዮጵያውያን ለአንድነትና ለነፃነት የከፈሉት መስዋዕትነት ፤ የኤርትራ ጥያቄ ፥ የፌደሬሽን አፈታትና የችግሮቹ ታሪካዊ ሂደትን አስመልክቶ "__ክህደት በደም መሬት__" በሰፊ ታሪካዊ ማስረጃዎች የተደገፈ ትንታኔውንና የራሱን ምስክርነት ይስጣል፡፡*

*አፄ ዮሐንስ፥ ራስ አሉላ ፥ አፄ ሚኒሊክና ኤርትራ ፥ ኤርትራና አድዋን ታሪካዊ ማስረጃዎችን እያነሳ ያወያያል፡፡ ቃኘው በኮሪያ፥ የኮንጎን፥ ኦጋዴንን ፥ ወልወልን፥ ዶጋሊ፥ ጉንደትና ጉራእን፥ ሃለይ ቆአቲትና ሰንአፌን የኢትዮጵያውያን አርበኝነት ትግሎች፥ የድልና የአሳዛኝ ፍጻሜዎችን ታሪክ ፤ እስከ ደርግ መንግሥት ውድቀት ድረስ የተደረጉ የታላላቅ ውጊያዎች--ዘመቻ አሉላ፥ የቀይ ኮከብ ዘመቻ፥ የቀይ ባህር ዘመቻ፥ የባህረ ነጋሽ ወዘተ..ታሪክ --እያነሳ ያስደምማል፡፡*

*በንጉሠ ነገሥቱና በደርግ መንግስታት የነበሩ ብዙ ባለስጣኖችና የጦር መኮንኖች ስምና ግብር በሰፊው የሚገኝበት ማህደር ነው፡፡ከሥር መሠረቱ የኢትዮጵያ ዘመናዊ መደበኛ ጦር ምስረታ ፥ ግንባታው፥ እድገቱና ውድቀቱ ብዙ ይተርካል፡፡ የምድር፥ የአየርና የባህር ኃይሎች አመሰራረት በመጨረሻም ውድቀታቸውን ፥ በተደረጉ አያሌ ጦርነቶች የተከፈለውም መስዋዕትነት መጠን አስመልክቶ በሰፊው ቀርቧል፡፡ ሰለ ሠራዊቱ የውጊያ ብቃት ፤ ሞራልና ያሳየው ጀግነት ብዙ ተብሎአል ፤ ተበዳይነቱንም ይናገራል፡፡ በተለይም እውነተኛውን የቅርብ ጊዜ ታሪካችንን ዛሬ በመንበረ ሥልጣን ላይ በተቀመጡ ታሪክ አጉዳፊዎችና ከሃዲዎች በሚሞነጫጨርና "የድል አድራጊዎች የታሪክ ብወዛና ቅልበሳ" ተረት ተረት ተወናብዶ ትውልድ እንዳይረሳቸው፥ አልፎም የሕሊና እና የመታሰቢያ ሐውልት እንዲሰራላቸው ይማፀናል፡፡ ስሜትን በእጅጉ ይቆሰቁሳል፤ ይቆጠቁጣል፤ ያስቆጫልም፡፡*

*ፀሐፊው ዳዊት ወ/ጊዮርጊስ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ሥፍራ ካላቸው ሰዎች አንዱ ናችው፡፡ የሐረር ጦር አካዳሚ 2ኛ ኮርስ ምሩቅ የሆኑት ሻለቃ ዳዊት በንጉሠ ነገሥቱ ዘመን በኤርትራ ክፍለ ሃገር በጦር አሰልጣኝነት ፥ በተዋጊነት፥ በአዝማች መኮንንነት ለበርካታ ዓመታት አገልግለዋል፡፡ ከደርግ መንግሥት ጋራ ቅራኔ ውስጥ ገብተው ሀገር ለመልቀቅ እሰከተገደዱበት ወቅት ድረስም በኤርትራ ክፍለ ሀገር የበላይ ኃላፊነት ፥ በምክትል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነት ፥ በእርዳታ ማስተባበርያና ማቋቋሚያ ዋና ኮሚሽነርነትና በሌሎችም ልዩ ልዩ መንግሥታዊ ኃላፊነት ቦታዎች ላይ ለበርካታ ዓመታት አገልግልዋል፡፡ ቀደም ሲል '__Red Tears__ " በሚል ርዕስ ሰለአብዮትና ረሀብ የጻፉት ሻለቃ ዳዊት አሁን ደግሞ የኢትዮጵያውያን ደም እንደ ጅረት የፈሰሰባትና ክህደት የተፈራረቀባት ኤርትራን ማዕከል አድርገው __ለሕዝብ ጆሮ አንግዳ የሆኑ፥ ከዚህ ቀደም ያልተነገሩና በቅጡ ያልተመዘገቡ ብዙ ጉዳዮችን በ "ክህደት በደም መሬት"__ መፅሐፋቸው ይዘው ብቅ ብለዋል ፡፡ ፀሐፊው በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያን ለሁለት ከፍለው በመግዛት ላይ የሚገኙት የአዲስ አበባውና የአስመራው አገዛዞች በሚነዙት የፈጠራ ታሪክ ሳቢያ እየተፈጠረ የሚገኘውን የታሪክ መዛባት ለመከላከል በመረጃ የተደገፉ በርካታ እውነታዎችን ያቀርባሉ፡፡ በእርግጥ በመፅሐፉ ወስጥ የሚገኙ አንዳንድ ነጥቦችና አመለካከቶች አነጋጋሪና አከራካሪ ውይይቶችን ሊያስነሱ ይችሉ ይሆናል፡፡ ይህም በጥልቀት ያልተፃፉ የታሪካችንን ምዕራፎች በበለጠ ለመገንዘብና ለማዳበር የበኩሉን አስተዋፅኦ ያደርጋል ብለን እናምናለን፡፡ "ማን ያውራ የነበረ ማን ያርዳ የቀበረ" ነውና __ክህደት በደም መሬት__ ብዙ ብዙ ታላላቅ ሀገራዊ ቁምነገሮችና የአያሌ ኢትዮጵያውያን ሕያው የጀግንነት ገድልና መስዋዕትነት ከታሪክ ማስረጃዎችና ከፀሐፊው የግል ገጠመኞች ጋር ተጣቅሰውና ተጣምረው የቀረቡበት ምንባብ ነው፡፡ ትውልድ ሊያመልጠው የማይገባ መጽሐፍ፡፡ ክህደት በደም መሬትን ያንብቡት፡፡ በቅርብ ቀናት ገበያ ላይ ይውላል፡፡ የገጽ ብዛት፡-470 ፤ ዋጋው $30 ፥ አሳታሚ፡- ኤዞፕ አሳታሚና አከፋፋይ፥* **Order Enquires can be sent to : Aesop Publishers & Distributors.** 43 Town & Country Drive Suite #119, PBM-230, Fredericksburg, va 22405. USA. Tel: (202) 386-3037. Number of pages: 470, Price: $30. Shipping and Handlingfor US and Canada add $2. Shipping and Handling for Europe and elsewhere add $4. Write your Check or Money order payable to __Aesop__.